የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.10
ADDIS ABABA 9th January, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፰/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ለዲላ-ቡሌ-ሃሮ ዋጬ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ............ገጽ ፲፪ሺ፺

## Content

Proclamation No.1168/2019

OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Dilla-Bulle-Harro Wachu Road Project Ratification Proclamation ..................................................................Page 12,090

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፰/፪ሺ፲፪

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለዲላ-ቡሌ-ሃሮ ዋጬ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፳፪ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሃያ ሁለት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ ኤፕሪል ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፱ በዋሽንግተን ዲ.ሲ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1168/2019

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

**WHEREAS,** the Loan Agreement, between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of Twenty Two Million United States Dollars (USD 22,000,000) for Financing Dilla-Bulle-Harro Wachu Road Project, was signed in Washington D.C on 13th day of April 2019;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of November, 2019;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ ‹‹ለዲላ-ቡሌ-ሃሮ ዋጬ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፰/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.አ.አ ኤፕሪል ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፱ በዋሽንግተን ዲ.ሲ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 13605 ፀድቋል፡፡

## ፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፪ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሃያ ሁለት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Dilla-Bulle-Harro Wachu Road Project Ratification Proclamation No.1168/2019".

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement Number 13605 signed in Washington D.C on 13th day of April 2019 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of Twenty Two Million United States Dollars (USD 22,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 9th day of January, 2020**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**